neighbor to neighbor MCPS

**2013–2014**

# ጎርቤት ለጎረቤት

## ተሳተፉ

ጎረቤት ለጎርቤት (N2N) ለMCPS ማህበረሰብ አባሎች አስፈላጊ በሆኑ የት/ቤት ስርአት ርእሶች የአነስተኛ ቡድን ውይይቶች ለማስተናገድ ወይም ለመሳተፍ እድል ይሰጣቸዋል። በዚህ አመት፣ በሁለት N2N ውይይቶች እድል ይኖራችኋል።

1. የMCPS ስራ ማስኬጃ በጀት፡- MCPS ወላጆችና የማህበረሰብ አባላት ከት/ቤት ዲስትሪክታቸው በጀት ውስጥ ለሚመጣው አመትና ከዚያ ባሻገርም ምኑን ዋጋ እንደሚሰጡት ማወቅ ይፈልጋል።
2. የደወል ሰአቶች- ዲስትሪክቱ በት/ቤት መጀመርያና መጨረሻ ሰአታት ለውጥ በቀረበው ሃሳብ—የደወል ሰአቶች ተብሎ የሚታወቀውም—በተማሪዎችና በማህበረሰቡ ምን ተፅእኖ እንደሚያስከትል የናንተን ሀሳብ ማወቅ ይፈልጋል።

በአንዱ ወይም በሁለቱ ርእሶች ለመሳተፍ መምረጥ ትችላላችሁ። በጉዳዩ ለመንቀሳቀስ የጎረቤት ለጎረቤት ድር ገፅ ጠቃሚ መረጃዎች ይዟል። የጎረቤት ከጎረቤት ድርጊት ማስተናገድ ወይም መሳተፍ ትፈልጋላችሁን? ልትወስዷቸው የምትችሉ የተወሰኑ እርምጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

**1 እርምጃ አንድ**

### አንድ ቡድን አሰባስቡና ቦታ ምረጡ።

የN2N ውይይት ለማስተናገድ ሁሉም ተጋብዟል። የተገኙ ተሳታፊዎች የመገልገያ አካል የሆኑትን ቪድዮዎችና ሰነዶችን ማየት እንዲችሉ፣ የኢንተርኔት አገልግሎት ያለው፣ ከተቻለ፣ ይመረጣል። ከመስመር ውጭ የቪድዮ ቅጂ ከፈለጋችሁ፣ ለpio@mcpsmd.org ኢሜይል አድርጉ።

**2 እርምጃ ሁለት**

### ቪድዮ ተመልከቱ ሰነዶችንም አገላብጣችሁ እዩ።

ቪድዮዎች ስለያንዳንዱ አርእስት ሰፋ የለ አስተያየት ያቀርቡላችኋል። ቪድዮዎቹ፣ ከሚታደሉት መፅሄቶች ጋር፣ ለውይይቶቻችሁ መሰረት ያቀርቡላችኋል።

**3 እርምጃ ሶስት**

### ተወያዩ።

ውይይታችሁን የምትጀምሩበት ሰአቱ አሁን ነው። በሁለቱም መገልገያዎች ውይይቱን ለማስጀመር መመርያ ጥያቄዎች ይዘዋል። አንድሰው ማስታወሻ መውሰዱን አረጋግጡ፣ ከፈለጋችሁም፣ ከMCPS ማህበረሰብ ጋር ለመጋራት የውይይታችሁን ጥቂት ፎቶግራፎች አንሱ።

**4 እርምጃ አራት**

### ሃሳቦቻችሁን ተጋሩ።

እባካችሁ ማስታወሻዎቻችሁንና ልታጋሩ የምትፈልጓቸውን የተወሰኑ ፎቶግራፎች በ pio@mcpsmd.org ኢሜይል አድርጉ። ለደወል ሰአቶች ውይይት፣ እባካችሁ አስተያየታችሁን በድር ገፅ መስመር ላይ በሚገኝ ፎርም ሞልታችሁ ገቢ አድርጉልን። ሁሉም አስተያየት ተሰባስቦ ከትምህርት ቦርድና ከበላይ ተቆጣጣሪ ጋር ይጋራል።

ለተጨማሪ መረጃና ለመጀመር ፣ *www.montgomeryschoolsmd.org* ጎብኙና "Neighbor to Neighbor"ን ፈልጉ።

ትርጉም፡- Language Assistance Services Unit • Division of ESOL Bilingual/Programs
የስርአተ ትምህርትና የትምህርት ፕሮግራሞች ፅ/ቤት

Montgomery County Public Schools
Rockville, Maryland
0661.14 • EGPS • Amharic